

Washington State Department of Health

ልዩ የጤና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ህፃናትና ወጣቶች

www.doh.wa.gov/cyshcn

# …የ COVID-19 ክትባት መረጃ

## ለተንከባካቢዎች የሚሰጥ መረጃ

- ክትባት ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላግቶቶች ላሏቸው ልጆች እና ወጣቶች (CYSHCN) በተለይ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም በ COVID-19 የመታመም ከፍተኛ ዕድል አላቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት ስር የሰደደ የጤና ሁኔታዎች እንዲሁም ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ጋር የቅርብ ንክኪ ስላላቸው ነው። ማስኮችን ማድረግ፣ እጆቻቸውን መታጠብ፣ እና ከሌሎች አስተማማኝ ርቀት መጠበቅ ላይ ችግር ሊኖርባቸውም ይችላል።

- የ Pfizer የ COVID-19 ክትባት ዕድሜያቸው 5 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ፍቃድ አግኝቷል።
- Centers for Disease Control and Prevention (CDC፣ የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል) እና የ American Academy of Pediatrics ለሁሉም ዕድሜያቸው 5 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የ COVID-19 ክትባትን ይመክራሉ።
- ዕድሜያቸው 5 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የመጨረሻ የክትባት ዶዛቸውን ከወሰዱ ከ 5 ወር በኋላ ማጠናከሪያ ክትባት መውሰድ አለባቸው።

- ደካማ በሽታ የመከላከል አቅም ያላቸው (እንግሊዘኛ ብቻ) ዕድሜያቸው 5 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ከሁለተኛ ክትባታቸው ከ 28 ቀናት በኋላ ተጨማሪ የ Pfizer ክትባት ዶዝ እንዲሁም የመጨረሻ ዶዛቸውን ተከትሎ ከወራት በኋላ ማጠናከሪያ ዶዝ መውሰድ አለባቸው። ይህ ምስል (እንግሊዘኛ ብቻ) ደካማ በሽታ የመከላከል አቅም ያለው ሰው እንደየዕድሜው ምን ያክል ጠቅላላ ዶዞች እንደሚያስፈልጉት ያሳያል።

- ክትባቱ ልጆችን እና ወጣቶችን ከ COVID-19 ለመጠበቅ በጣም አስተማማኝ እንዲሁም ውጤታማ ነው።

## ልጆች መከተብ ለምን ያስፈልጋቸዋል?

- ክትባት መውሰድ ልጆችን በትምህርት ቤት እንዲሁም ከጓደኞቻቸው እና ቤተሰብ ጋር ሲሆኑ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ይረዳል። ክትባት የወሰዱ ልጆች COVID-19 ቢይዛቸው በከባድ ህመም የመታመም፣ ሆስፒታል ውስጥ የመግባት፣ ወይም የመሞት ዕድላቸው በጣም ዝቅተኛ ይሆናል።

- በ COVID-19 የታመሙ ልጆች “ረዥም COVID-19” ን ጨምሮ የአጭር እና የረዥም ጊዜ የጤና እክሎች (እንግሊዘኛ ብቻ) ሊያሳዩ ይችላሉ። የተወሰኑት እክሎች፣ መልቲ ሲስተም ኢንፍላማቶሪ ሲንድረም (MIS-C) (እንግሊዘኛ ብቻ) የመሳሰሉ፣ ከባድ እንዲሁም ሆስፒታል ውስጥ መግባት እና ሞትም ጭምር ሊያስከትሉ ይችላሉ። ክትባት ልጆችን ጤናማ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ ለማድረግ ምርጡ መንገድ ነው።

## CYSHCN በከባድ የ COVID-19 ህመም የመታመም ዕድል ሊኖራቸው ይችላል

- ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያላቸው ወይም የተወሰነ የህክምና ሁኔታዎች (እንግሊዘኛ ብቻ) ያላቸው ልጆች በ COVID-19 ቢያዙ በጣም በከባዱ የመታመም ሰፊ ዕድል ሊኖራቸው ይችላል። ክትባት ልጆችን ከ COVID-19 ለመጠበቅ ወሳኝ መንገድ ነው።

- ልጆችን ለመጠበቅ ወሳኙ መንገድ በቤተሰቡ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎች ሙሉ ክትባቱን እና አበረታች መውሰዳቸውን ማረጋገጥ ነው። ይህም ማለት ወላጆች እና ተንከባካቢዎችም ክትባት መውሰዳቸው አስፈላጊ ነው ማለት ነው።

## የ COVID-19 ክትባት ለ CYSHCN ደህንነቱ የተጠበቀ ነው

- ስር የሰደዱ የህክምና ሁኔታዎች ያሏቸው ልጆች እና አዋቂዎች የ COVID-19 ክትባት ማግኘት ይችላሉ።
- አንድ ሰው ክትባት የማይወሰድበት ብቸኛው ምክንያት ለማንኛውም የ የ COVID-19 ክትባት ንጥረ ነገሮች ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል ግብረ መልስ (epi pen የሚያስፈልገው ግብረ መልስ) ከነበራቸው ነው።
- የክትባት ጥቅሞች በ COVID-19 በመያዝ ከሚመጡ አደጋዎች የበለጠ ሚዛን ይደፋሉ።
- ስለ ክትባቱ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካልዎት የልጅዎን የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ያነጋግሩ።

## የጎንዮሽ ጉዳቶች

በ COVID-19 የመታመም የጤና አደጋዎች ከክትባቱ የጎንዮሽ ጉዳቶች የበለጡ ናቸው።
ልጆች ክትባት ከወሰዱ በኋላ የተወሰኑ የጎንዮሽ ጉዳቶች መሰማታቸው የተለመደ ነው። በብዛት የተለመዱት የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የቆሰለ ክንድ
- የጡንቻ ሕመም
- የድካም ስሜት
- የራስ ምታት
- ትኩሳት
- ብርድ፣ ብርድ ማለት

ልጅችዎ የጎንዮሽ ጉዳቶች ካሏቸው እንዴት ምቾት እንዲሰማቸው እንደሚያደርጉ የልጅዎን የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ይጠይቁ። ጸጥታ በተሞላባቸው ተግባራት ምቾት እንዲሰማቸው ማድረግም ይችላሉ። አብዛኞቹ የጎንዮሽ ጉዳቶች በአንድ ወይም በሁለት ቀናት ውስጥ ይጠፋሉ።

ልጅዎ ለሌሎች ክትባቶች ከባድ የአለርጂ ግብረ መልስ ከነበረው፣ አሁንም የ COVID-19 ክትባት መውሰድ ይችላሉ። የጤና እንክብካቤ አቅራቢው ከክትባቱ በኋላ ማንኛውንም አይነት ፈጣን ግብረ መልሶች ለመከታተል እስከ 30 ደቂቃ እንዲቆዩ ይጠይቃቸዋል።

ለ COVID-19 ክትባት ከባድ ግብረ መልስ የማጋጠም ዕድል በጣም ዝቅተኛ ነው። ከ COVID-19 ህመም በኋላ ከባድ ምልክቶች የማየት ዕድል ከክትባት በኋላ ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ከማየት እድል ይልቅ በጣም ከፍተኛ ነው። ሊከሰቱ ስለሚችሉ የ COVID-19 ክትባት ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች እዚህ ጋር የበለጠ ይወቁ።

**የ COVID-19 ክትባትን ካገኙ በኋላ ድንገተኛ የህክምና አደጋ ካጋጠምዎ፤ ወዲያውኑ ወደ 9-1-1 ይደውሉ።**

## ህፃን ልጄን እንዴት ማስከተብ እችላለሁ?

የ COVID-19 ክትባት ካላቸው የህጻናት ሀኪምዎን ይጠይቁ። ከሌላቸው፣ የእኛን የክትባት አመልካች መጠቀም ይችላሉ።

## ድጋፎችን መጠየቅ

ቀጠሮ ሲይዙ ወይም በክትባት ጣቢያው ሲደርሱ፣ ልጅዎ የተወሰነ ተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ ሰራተኞቹ እንዲያውቁ ያድርጉ። ለምሳሌ፣ ምናልባት ማስክ ማድረግ ወይም ከክትባቱ በኋላ መቀመጥ እና መጠበቅ የማይችሉ ናቸው። ምናልባት ደማቅ ብርሃኖች እና ጩኸት ያላባቸው ክፍሎች ያስቸግሯቸዋል። የሚከተሉትን የመሳሰሉ ድጋፎችን መጠየቅ ይችላሉ፡-

- ከክትባቱ በኋላ ከመቀመጥ ይልቅ ዞር ዞር ማለት።
- አቅራቢው ልጅዎን በመኪናዎ ውስጥ እንዲከትበው ማድረግ።
- በቀጠሮው ወቅት የልጅዎ ተወዳጅ ሰው አብሯቸው እንዲሆን ማድረግ።
- የህዝብ ጭንቅንቅ ካልባቸው ቦታዎች ርቀው ጸጥ ባለ ክፍል ውስጥ ልጅዎ እንዲከተቡ ማድረግ።

ልጅዎ ከቤት የመውጣት ችግሮች ካሉበት፣ ልጅዎ በቤት ውስጥ እንዲከተብ ተንቀሳቃሽ የክትባት ቡድን ጋር ይገናኙ።

## ተጨማሪ መረጃ የት ማግኘት እችላለሁ?

ህጻናትን ለ COVID-19 መከተብ ላይ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት፣ VaccinateWA.org/Kids ን ይጎብኙ።

ሌሎች ሀብቶች፡-

- በወረርሺኝ ወቅት ለ CYSHCN የሚደረግ እንክብካቤ ላይ የ American Academy of Pediatrics መምሪያ
- የ COVID-19 ግብዓቶች ለ CYSHCN ከ Lucile Packard Foundation
- የ COVID-19 መረጃ እና ድጋፍ ከ Informing Families.
- የ Department of Health የ COVID-19 ክትባት የተግባቦት ካርድ የ Center for Dignity in Healthcare for People with Disabilities ማህበራዊ ታሪክ ስለ ክትባቱ ልጁ ወይም ወጣቱ ጋር ለመግባባት ሊረዱ ይችላሉ።
- የ BLIND COVID Access የስልክ መስመር (360-947-3330) ማየት የተሳናቸው እና ዝቅተኛ ዕይታ ያላቸው ሰዎች COVID-19 ጋር ስለተያያዙ ሀብቶች ተደራሽነት ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ ያስችላቸዋል። BLINDCOVID.com የክትባት ምርመራ፣ የክትባት ጣቢያዎች፣ እና በወረርሺኝ ወቅት ዕለታዊ ህይወትን መቃኘት ላይ ተጨማሪ ሀብቶች እና ተግባቦት ያዘጋጃል።
- ከ CYSHCN ጋር ግንኙነት ላላቸው ጥያቄዎች፣ እባክዎ ኢሜይል በ cyshcn@doh.wa.gov ይላኩ።

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም ኢሜይል በ civil.rights@doh.wa.gov ይላኩ።